የሒሳብ ትምህርት ይዘት ምጠና መመሪያ

ሒሳብ 1ኛ - 6ኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

ታህሳስ 2013 ዓ.ም

የሒሳብ ትምህርት ይዘት ምጠና ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል

1. መግቢያ

በ2013 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮሮና (COVID 19) በሽታ ወረርሽን ምክንያት መጋቢት ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ መቋረጡ እና ከ8ኛ እና 12 ክፍል ተማሪዎች በስተቀር የሌሎች ክፍል ተማሪዎች በነጻ ዝውውር ወደሚቀጥለው ክፍል መዛወራቸው ይታወሳል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የትምህርት ሚኒስቴር የዓለም አቀፉ የጤና ድርጅት እና ከኢትዮጵያ የጤና ሚኒስቴር በሽታውን መቆጣጠር ሲቻል የገጽ ለገጽ ትምህርት ትምህርት እንደሚጀመር ተገልጿል።

ስለሆነም የኢፌዲሪ. የጤና ሚኒስቴር የኮሮና በሽታ ወረርስኝ ፕሮቶኮልን በጠበቀ መልኩ ትምህርት መቀጠል እንደሚቻል ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ባቀረበው ምክረ ሀሳብ መሰረት በከተማችን የገጽ ለገጽ ትምህርት ይጀመራል። በዚህ ሂደትም ካለፈው ዓመት የትምህርት ርዕሶች ያልተሸፈኑትን በማካካሻ መልክ ለ45 ቀናት እንዲሰጡ ተደርጓል።

በ2013 ዓ.ም የሚሰጠው ትምህርት የማካካሻ ክፍለ ጊዜያት ሲቀነሱለት የሚያጥር ስለሆነ በ2013 ዓ.ም. የሚሰጠው ትምህርት ክፍለ ጊዜያት አነስተኛ ስለሚሆን የይዘት ምጣኔ መስራት አስፈላጊ በመሆኑ ይሕ የይዘት ምጣኔ መመሪያ ተዘግጅቷል።

2. አስፈላጊነት

የይዘት ምጣኔ መስራት ያስፈለገበት ምክንያት :

- በጣም አስፈላጊ እና መቅረት የሌለባቸውን ይዘቶች ለመወሰን
- በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተመሳሳይ ይዘቶችን ማስተማር አንዲቻል።

3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች

- የመመሪያውን አስፈላጊነት ለመግለጽ
- የይዘት ምጠና የተከናወነበትን አበይት ጉዳዮች ለማሳየት
- በየክፍሉ የተሰሩትን የይዘት ምጣኔዎች እና ይዘቶች ለማስተዋወቅ

4. የታዩ ዓበይት ጉዳዮች

የ2013 ዓ.ም ትምህርት በሁለት ደረጃዎች ይከፈታል። የመጀመሪያው ለግል ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርት የሚጀመርበት ቀን ሕዳር 21 ቀን ሲሆን የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ5ኛ ክፍል በላይ ያሉት ሕዳር 28 ቀን 2013 ዓ.ም ይጀምራሉ።

በነዚህ ወቅት ያለፉት እና ያልተሸፈኑት የትምህርት ርዕሶች ለ45 ቀናት መሸፈን አለባቸው። ስለሆነም ቀሪው ጊዜ አጭር ይሆናል። ስለሆነም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ጥምህርቱን ለመሸፈን ይህንን ይዘት ምጣኔ መስራት አስፈልጓል።

5. የይዘት መመጠኛ መስፈርቶች

ይዘትን ለመመጠን ይዘቶቹ ለሌሎች የትምህርተ ዓይነቶቻ ያላቸው ተፈላጊነት እና ቅድመ ሁኔታነት፣ ለነባራዊው ዓለም ያላቸው ተፈላጊነት እና ለቀን ተቀን አገልግሎት ባላቸው ተመራጭነት፣ አዲስ ሀሳብ መሆናቸው እና በሌሎች ክፍሎቻ ያላቸው ተደጋጋሚነት፣ ተማሪዎቹ ይዘቱን በቀላሉ ለመረዳት ያላቸው አስተዋጽዖ እና ይዘቶቹ በዚሁ ክፍል ውስጥ በሌሎች ምዕራፎች ውስጥ በጥልቀት መቅረባቸው እየታየ ጥቅም ላይ ውሏል።

6. የተመጠኑ ይዘቶች

1ኛ ክፍል

ምዕራፍ	የምዕራፉ ርዕስ	ክፍለ ጊዜ	የተከለሰ ክፍለ ጊዜ
1	እስከ 9 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮች	20	4
2	እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	22	4
3	ከ0 እስከ20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች	12	2
4	እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	17	4
5	ባህላዊ የመለኪያ ምድቦችን በመጠቀም መለካት	9	2
6	የክፍልፋዮች ጽንሰ ሀሳብ መግቢያ	6	1
7	እስከ 20 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትና ማካፈል	22	4
8	መስመሮችና ቀላል ምስሎች	10	2
9	እስከ መቶ ያሉ ሙሉ ቁጥሮች	18	4
10	የኢትዮጵያ ገንዘቦች	5	1
11	ጊዜ	5	1
12	መረጃ አያያዝና ቀላል ሂሳባዊ ድርድሮች	5	1
ጠቅላላ ድምር		**151**	**30**

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
1	**ምዕራፍ 1**፡- እስከ 9 ያሉ የመቁጠሪያ ቁጥሮች	4	1.1 ከ1 እስከ 5ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸው	2
			1.2 ከ6 እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸው	2
2	**ምዕራፍ 2**፡- እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	4	2.1 ድምራቸው ከ 9 ያልበለጡ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መደመር	2
			2.2 እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን መቀነስ	2
3	**ምዕራፍ 3**፡- ከ0 እስከ20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች	2	3.1 ዜሮ ቁጥር	1
4	**ምዕራፍ 4፡-** እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	4	4.1 ድምራቸው ከ20 ማይበልጡ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር	2
			4.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉቁጥሮችን መቀነስ	1
			4.3 መደመር እና የመቀነስ ፕሮብሌሞች	1
5	**ምዕራፍ 5**፡-ባህላዊ የመለኪያ ምድቦችን በመጠቀም መለካት	2	5.1 የርዝመት ልኬት	1
			5.2 የይዘት ልኬት	1
6	**ምዕራፍ 6**፡- የክፍልፋዮች ጽንሰ ሀሳብ መግቢያ	1	6.1 ግማሽ	1
7	**ምዕራፍ 7፡-** እስከ 20 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትና ማካፈል	4	7.1 እስከ 20 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማባዛት	2
			7.2 እስከ 20 ያሉ ተጋማሽ ቁጥሮችን በ 2 ማካፈል	2
8	**ምዕራፍ 8፡-** መስመሮችና ቀላል ምስሎች	2	8.1 ቀጥታና ጥምዝ መስመሮች	1
			8.2 ቀላል ምስሎች	1
9	**ምዕራፍ 9፡-** እስከ መቶ ያሉ ሙሉ ቁጥሮች	4	9.1 የ10 ብዜቶች እስከ 100	1
			9.2 ከ21 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች	1
			9.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል	1
			9.4 እስከ መቶ ያሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ	1
10	**ምዕራፍ 10**፡- የኢትዮጵያ ገንዘቦች	1	10.1 የኢትዮጵያ ሳንቲሞችና የብር ኖቶች	1
11	**ምዕራፍ 11፡-** ጊዜ	1	11.1 በቀን ውስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያት	1
12	**ምዕራፍ 12፡-** የመረጃ አያያዝና ቀላል ሒሳባዊ ድርድሮች	1	12.1 ቀላል ስዕላዊ ግራፎች	1

2ኛ ክፍል

ምዕራፍ	የምዕራፉ ርዕስ	ክፍለ ጊዜ	የተከለሰ ክፍለ ጊዜ
1	እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	54	11
2	ማባዛትና ማካፈል እስከ 100	40	8

3	ልኬት	10	2
4	የክፍልፋዮች ጽንሰ ሃሳብ መግቢያ	6	1
5	ሙሉቁጥሮች እስከ 1000	12	2
6	ነጥቦች፣ ቀጥታ መስመሮች እና ቅርጾች(ምስሎች)	14	3
7	ገንዘብ	4	1
8	ጊዜ	4	1
9	መረጃ አያያዝና ድርድር	6	1
	ጠቅላላ ድምር	**150**	**30**

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
1	**ምዕራፍ 1፡-** እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	11	1.1 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ክለሳ	1
			1.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ክለሳ	1
			1.3 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥርን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር ጋር ያለ አለኝታ እና ያለብድር መደመርና መቀነስ	1
			1.4 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥርን ከባለ ሁለት አሃዝ በአለኝታና በብድር መደመርና መቀነስ	2
			1.5 ሁለት ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ እና ያለብድር መደመርና መቀነስ	2
			1.6 ሁለት ባለ ሁለት ዘሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታና በብድር መደመርና መቀነስ	3
			1.7 በመደመር እና በመቀነስ እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች የሚሰሩ የቃላት ፕሮብሌሞች	1
2	**ምዕራፍ 2፡-** ማባዛትና ማካፈል እስከ 100	8	2.1 ያለ ቀሪ በ 2 እና በ 10 ማባዛትና ማከፈል ክለሳ	2
			2.2 በ0 እና በ1 ማባዛት እና ለ1 ማካፈል	4
			2.3 ማባዛትና ማካፈል በ3፣4፣5፣6፣7፣8 እና 9	2
3	**ምዕራፍ 3፡-** ልኬት	2	3.1 ርዝመትን በሳንቲ ሜትርና በሜትር መለካት	1
			3.2 በሳንቲ ሜትርና በሜትር የተገለጹ ርዝመቶችን መደመርና መቀነስ	1
4	**ምዕራ 4፡-** የክፍልፋዮች ጽንሰ-ሀሳብ መግቢያ	1	4.1 ግማሽና ሩብ ክፍልፋዮችን ክለሳ	1
5	**ምዕራፍ 5**፡- ሙሉቁጠሮች እስከ 1000	2	5.1 የ100 ብዜቶች	1
			5.2 ሙሉ ቁጥሮች ከ101-1000	1
6	**ምዕራፍ 6**፡- ነጥቦች	3	6.1 ማስመሪያ በመጠቀም ቀጥታ መስመሮችን	1

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
	ቀጥታ መስመሮች እና ቅርጾች(ምስሎች)		መሳል	
			6.2 ጎነ አራ፣ካሬ፣ጎነሶስት እና ክብ ምስሎች	2
7	**ምዕራፍ 7**፡- ገንዘብ	1	7.2 ግብይት	1
8	**ምእራፍ 8**፡- ጊዜ	1	8.2 ሰዓትና ደቂቃ	1
9	**ምዕራፍ 9**፡- መረጃ አያያዝና ድርድር	1	9.1 ቀላል መረጃዎችን መሰብሰብ	1

3ኛ ክፍል

ምዕራፍ	የምዕራፉ ርዕስ	ክፍለ ጊዜ	የተከለሰ ክፍለ ጊዜ
1	እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸው	27	5
2	ልኬት	14	3
3	ክፍልፋዮች	12	2
4	እስከ 10,000 ያሉ ሙለሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	28	6
5	እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማባዛትና ማከፈል	37	8
6	መስመሮችና ቀላል ምስሎች	16	3
7	ገንዘብ	5	1
8	ጊዜ	6	1
9	መረጃ አያያዝ	5	1
	ጠቅላላ ድምር	**150**	**30**

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
1	**ምዕራፍ1**፡- እስከ 10,000 የሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸው	5	1.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉቁጥሮ ክለሳ	1
			1.2 እስከ 1000 ባሉ ሙሉቁጥሮች የማስላት ክለሳ	1
			1.3 የ100 እና የ1000 ብዜቶች እስከ 10,000 ባሉ ሙሉቁጥሮች	1
			1.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮች	1
			1.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ	1
2	**ምዕራፍ 2**፡- ልኬት	3	2.1 ርዝመትን በሚሊሜትር፣በሳንቲ ሜትር እና በኪሎ ሜትር መለካት	1
			2.2 ይዘትን በሚሊሊትር(ሚ.ሊ) እና በሊትር(ሊ) መለካት	1
			2.3 ክብደትን በግራም(ግ)፣በኪሎ ግራም(ኪ.ግ) እና በኩንታል መለካት	1

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
3	**ምዕራፍ 3**፡-ክፍልፋዮች	2	3.2 ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋች	1
			3.4 ቀላል ክፍልፋዮችን ማወዳደር	1
4	**ምዕራፍ 4**፡- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	6	4.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮን መደመር	3
			4.2 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን መቀነስ	
5	**ምዕራፍ 5**፡- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችና ማባዛትና ማካፈል	8	5.1 የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት	1
			5.2 የ1000 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት	1
			5.3 የማባዛት ውጤታቸው ከ10,000 ያልበለጡ የሙሉ ቁጥሮችና የባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ውጤት	2
			5.4 እስከ 10,000 ያሉ የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮና በ10 ማካፈል	1
			5.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች እና በ 10 በቀሪና ያለቀሪ ማካፈል	3
6	**ምዕራፍ 6፡-** መስመሮችና ቀላል ምስሎች	3	6.2 ተቋራጭ፣ ትይዩና ቀጤ ነክ ተቋራጭ መስመሮች	1
			6.3 ሬክታንግል፣ ካሬ፣ ፓራሌሎግራምና ትራፒዚየም	2
7	**ምዕራፍ 7፡-** ገንዘብ	1	7. 1 የገንዘብ ኖቶችን መዘርዘር(መቀየር)	1
8	**ምዕራፍ 8፡-** ጊዜ	1	8.2 ሰዓትና ደቂቃ	1
9	**ምዕራፍ 9፡-** መረጃ አያያዝ	1	9.1 ቀላል የምስል ግራፎች	1

4ኛ ክፍል

ምዕራፍ	የምዕራፉ ርዕስ	ክፍለ ጊዜ	የተከለሰ ክፍለ ጊዜ
1	ሙሉ ቁጥሮች እስከ 1,000,000	25	5
2	እስከ 1,000,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ላይ አራቱ የሂሳብ ስሌቶች	41	8
3	ክፍልፋዮችና አስርዮሻዊ ቁጥሮች	27	5
4	ልኬት	18	4
5	የጠለል ምስሎችና ጠጣር ምስሎች	20	4
6	ጊዜ	9	2
7	መረጃ አያያዝ	10	2
	ጠቅላላ ድምር	**150**	**30**

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
1	**ምዕራፍ 1**፡- ሙሉ ቁጥሮ እስከ 1,000,000	5	1.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁትሮችን ክለሳ	1
			1.3 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮ	1
			1.4 የቁጥር ቤት ዋጋ በባለ 8 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች	1
			1.5 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ	1
			1.6 የቁጥሮችን አቅራብ ዋጋዎች በማጠጋጋት መፈለግ	1
2	**ምዕራፍ 2**፡- እስከ 1,000,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ላ አራቱ የሂሳብ ስሌቶች	8	2.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	2
			2.2 ብዜታቸው ከ1,000,000የሚያንሱ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት	3
			2.3 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥርና በ10 ማካፈል	3
3	**ምዕራፍ 3**፡- ክፍልፋዮችና አስርዮሻዊ ቁጥሮች	5	3.1 ክፍልፋዮች የአንድ ሙሉ ነገር ክፍሎች	1
			3.4 አቻ ክፍልፋዮች	1
			3.5 አስረኛ፣ መቶኛ እና አስርዮሽ ቁጥሮች	1
			3.6 እስከ ሁለት አስርሽ የቁጥር ቤቶች ያላቸው አስርዮሻዊ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ	1
			3.7እስከ ሁለት አስርዮሻዊ የቁጥር ቤቶች ያላቸው አስርዮሻዊ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	1
4	**ምዕራፍ 4**፡- ልኬት	4	4.1 ርዝመትን መለካት	2
			4.2 ክብደትን መለካት	1
			4.3 ይዘትን መለካት	1
5	**ምዕራፍ 5፡-** የጠለል ምስሎችና ጠጣር ምስሎች	4	5.1 ማዕዘናዊ አንግል	1
			5.2 ነጥቦች፣ ቀጥታ መስመሮችና ጠለሎች	1
			5.3 የሬክታንግልና ካሬ ዙሪያና ስፋት	1
			5.4 ጠጣር ምስሎች	1
6	**ምዕራፍ 6**፡- ጊዜ	2	6.1 ሰዓት፣ ደቂቃና ሴኮንድ	1
			6.2 ስሌቶች በጊዜ መስፈሪያ ምድቦች ላይ	1
7	**ምዕራፍ 7፡-** መረጃ አያያዝ	2	7.1 የመረጃዎችን ባር ግራፍ መስራት	1

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
			7.2 የባር ግራፎችን መተርጎም	1

5ኛ ክፍል

ምዕራፍ	የምዕራፉ ርዕስ	ክፍለ ጊዜ	የተከለሰ ክፍለ ጊዜ
1	ሙሉ ቁጥሮችእና አራቱ መሠረታዊ ስሌቶች	48	9
2	በተለዋዋጮች መስራት	24	4
3	ክፍልፋዮች፣ አስርዮሾችና አራቱ መሰረታዊ ስሌቶች	42	7
4	መረጃ አያያዝ	14	2
5	ጂኦሜትራዊ ምስሎችና ልኬት	42	8
	ጠቅላላ ድምር	**170**	**30**

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
1	**ምዕራፍ 1፡-** ሙሉ ቁጥሮ እና አራቱ መሰረታዊ ስሌቶች	9	1.1 ከ1,000,000 የሚበልጡ ሙሉ ቁጥሮች	5
			1.2 መሰረታዊ ስሌቶች በሙሉ ቁጥሮች ላይ	4
2	**ምዕራፍ2፡-** በተለዋዋጮች መስራት	4	2.1 አልጀብራዊ ቁሞችና መግለጫዎች	3
			2.2 የእኩልነትና ያለእኩልነት አረፍተ ነገሮች	1
3	**ምዕራፍ 3፡-** ክፍልፋዮች፣ አስርዮሾችና አራቱ መሰረታዊ ስሌቶች	7	3.1 የክፍልፋይ አይነቶች	1
			3.2 መቶኛን(ፐርሰንትን) በክፍልፋይ መግለጽ	1
			3.3 ክፍልፋዮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል መጻፍ	1
			3.4 መሰረታዊ ስሌቶችና ክፍልፋዮች	2
			3.5 አስርዮሾችና ማስላት	2
4	**ምዕራፍ 4፡-** መረጃ አያያዝ	2	4.1 ባር ግራፎችን መስራትና መተርጎም	1
			4.2 የቁጥሮች አማካይ	1
5	**ምዕራፍ 5፡-** ጂኦሜትራዊ ምስሎችና ልኬት	8	5.2 አንግሎችና ልኬቶቻቸው	1
			5.3 ጎነ ሶስት ምስሎችን በጎናቸውና በአንግላቸው መመደብ	2
			5.4 ምጥጥን መስመሮ	4

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
			5.5 ልኬት	1

6ኛ ክፍል

ምዕራፍ	የምዕራፉ ርዕስ	ክፍለ ጊዜ	የተከለሰ ክፍለ ጊዜ
1	የስብስብ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች	19	3
2	የሙሉ ቁጥሮች ተካፋይነት	23	4
3	ክፍልፋዮና አስርዮሽ ቁጥሮች	41	7
4	ድፍን ቁጥሮች	18	3
5	መስመራዊ የእኩልነትና ያለእኩልነት ዐረፍተ ነገሮችና ወደረኛነት	25	5
6	ጂኦሜትሪ እና ልኬት	44	8
	ጠቅላላ ድምር	**170**	**30**

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
1	**ምዕራፍ 1፡-** የስብስብ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች	3	1.2 የስብስቦች ዝምድና	1
			1.3 የስብስብ ስሌቶች	2
2	**ምዕራፍ 2፡-** የሙሉ ቁጥሮች ተካፋይነት	4	2.1 የተካፋይነት ጽን ሃሳብና የተካፋነት ደንደቦች	1
			2.2 ብዜቶችና አካፋዮች	3
3	**ምዕራፍ 3፡** -ክፍልፋዮና አስርዮሽ ቁጥሮች	7	3.1 ክፍልፋዮችን በዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል መግለጽ	1
			3.2 ክፍልፋዮችን ወደ አስርዮሽ ቁጥሮችና መቶኛዎ መቀየር	2
			3.3 ክፍልፋዮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ	1
			3.4 ክፍልፋይ ቁጥሮችንና አስርዮሽ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ	1
			3.5 ክፍልፋዮችንና አስርዮሽ ቁጥሮችን ማባዛትና ማካፈል	2
4	**ምዕራፍ 4፡-** ድፍን ቁጥሮች	3	4.1 ድፍን ቁጥሮችን ማስተዋወቅ	1
			4.2 ድፍን ቁጥሮችን ማወዳደርና	1

ቁ	ምዕራፍ	ክፍለ ጊዜ	የተመጠነ ንዑስ ርዕስ	የተመጠኑ ክፍለ ጊዜያት
			በቅደም ተከተል መጻፍ	
			4.3 ድፍን ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ	1
5	**ምዕራፍ 5፡-** መስመራዊ የእኩልነትና ያለእኩልነት ዐረፍተ ነገሮችና ወደረኛነት	5	5.1 የመስመራዊ የእኩልነትና ያለእኩልነት ዓረፍተ ነገሮችና ወደረኛነት	1
			5.2 ነጥቦችን በስርዓተ መዋቅር ላይ ማመልከት	1
			5.3 ወደረኛነት	3
6	**ምዕራፍ 6፡-** ጂኦሜትሪ እና ልኬት	8	6.1 አንግሎች	2
			6.2 ጎነ ሶስቶችን መንደፍ	2
			6.3 ልክክ(ተጋጣሚ) ጎነ ሶስቶች	3
			6.4 ልኬት	1

7. የመምህሩ እና የተማሪው ሚና

መምህራን ቀሪ ክፍለ ጊዜያትን በአግባቡ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎችም ሁሉንም ክፍለ ጊዜያት በአግባቡ ክፍል በመገኘት መማር፣ በመጽሃፉ የተቀመጡ ሁሉንም ይዘቶች በግላቸው የማንበብ ፣መምህራኑ የሚሰጧቸውን ተጨማሪ መልመጃዎች የመስራት እና ሌሎች አጋዥ መጻህፍትን በማንበብ ራሳቸውን ብቁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።